የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፷
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፪ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 60
ADDIS ABABA, 7th September, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፭/፪ሺ፲፰
የኢትዮጵያ የስታቲስቲክስ አዋጅ.....
.....ገጽ ፳ሺ፪፻፶፪

Content

Proclamation No. 1435/2026
Ethiopian Statistics Proclamation……..
.....Page 20252

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፭/፪ሺ፲፰ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አዋጅ

የልማት ዕቅድን፣ የፖሊሲ ቀረጻን እና የብሔራዊ ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራሞችን ለመደገፍ እንዲቻል፤ ከፍተኛ ጥራት ያለው፣ ወቅታዊ እና አስተማማኝ የስታቲስቲክስ ዳታዎች እንዲመነጩ፣ እንዲቀናጁና እንዲሰራጩ የሚያደርግ ዘመናዊ፣ የተቀናጀና በሠለጠነ መንገድ የሚመራ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቦርድ ስልታዊ አመራር የሚሰጥበት፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የፖሊሲ አቅጣጫና የቁጥጥር ተግባራትን የሚያከናውንበትን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት በሁሉም የስታቲስቲክስ ሥራዎቹ ሂደት ላይ የቴክኒክ ሥልጣን እንዲኖረው የሚያደርግ ግልጽ ተቋማዊ ማዕቀፍ መዘርጋት በማስፈለጉ፤

PROCLAMATION No. 1435/2026

ETHIOPIAN STATISTICS PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to establish a modern, integrated, and well-governed National Statistical System that ensures the production, coordination, and dissemination of high quality, timely, and reliable statistical data to support development planning, policy formulation, and national transformation programs;

WHEREAS, it has become necessary to establish a clear institutional framework whereby a Board provides strategic leadership, the Ministry of Planning and Development carries out policy direction and regulatory functions, and the Ethiopian Statistical Service exercises technical authority over all of its own activities throughout the statistical lifecycle;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት ባለድርሻ አካላትን ሚና እና ኃላፊነት የሚደነግግ፣ ሞያዊ ነፃነትን የሚያረጋግጥ፣ ተቋማዊ አቅምን የሚያጠናክር፣ እንዲሁም ተስማሚ የሆኑ ደረጃዎችን፣ ምደባዎችን፣ ሜታ ዳታዎችን እና የስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን በመጠቀም የሥራ ድግግሞሽንና እርስ በእርስ የሚጋጩ ዳታዎችን የሚያስቀር አጠቃላይ እና ወጥ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ተጠያቂነትን፣ ግልጽነትን እና ሙያዊ ታማኝነትን ለማጎልበት፣ በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ የቁጥጥር፣ የክንውን እና የክትትል ተግባራት መካከል ግልጽ የሆነ የሚና ክፍፍል መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓቱን ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሠረታዊ የኦፊሻል ስታቲስቲክስ መርሖዎች እና ከአፍሪካ የስታቲስቲክስ ቻርተር እንዲሁም ከሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸው መርሖዎች እና መስፈርቶች ጋር ማጣጣም አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is essential to provide a comprehensive and coherent legal framework that clearly defines the roles and responsibilities of stakeholders within the National Statistical System, ensures professional independence, strengthens institutional capacity, and avoids duplication of efforts and conflicting data through the use of harmonized standards, classifications, metadata, and statistical systems;

WHEREAS, it is necessary to ensure a clear separation of roles between regulatory, operational, and oversight functions within the National Statistical System, in order to enhance accountability, transparency, and professional integrity;

WHEREAS, it is necessary to align the National Statistical System with the United Nations Fundamental Principles of Official Statistics, the African Charter on Statistics, and other internationally accepted principles and standards;

ነባሩ የሕግ ማዕቀፍ የሆነው የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፪/፩ሺ፱፻፺፯ እንዲሁም የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ የተካተቱት የስታቲስቲክስ አንቀጾች፣ እንደ ጂኦስፓሻል፣ ዲጂታል፣ በሴንሰር ላይ የተመሠረቱ እና የቢግ ዳታ ቴክኖሎጂዎችን ጨምሮ አዳዲስ የመረጃ ምንጮችን ለማስተናገድ በቂ ሆነው ባለመገኘታቸው፣ እንዲሁም በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥን ለማጎልበት በዳታ ሳይንስ ረገድ የሚታዩ የፈጠራ ሥራዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት የሌለው በመሆኑ፤

WHEREAS, the existing legal frameworks, the Central Statistics Authority Establishment Proclamation No. 442/2005, as well as the statistical provisions included in the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021, are inadequate to address emerging data sources, including geospatial, digital, sensor-based, and big data technologies, and lack mechanisms to harness innovations in data science for evidence-based decision-making;

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ኦፊሽያል ስታቲስቲክስን የማመንጨት እና የማሰራጨት ኃላፊነት የተጣለበት ራሱን የቻለ፣ ሞያዊ ነፃነት ያለው ዋና ተቋም ሆኖ ዕውቅና እንዲሰጠው እና እንዲጠናከር ማድረግ፤ እንዲሁም ተቋሙ ከሌሎች የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት አባላት ጋር በመሆን ተግባሩን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘና ብቁ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it has become necessary to recognize and strengthen the Ethiopian Statistical Service as an autonomous principal institution with professional independence entrusted with the production and dissemination of official statistics, and to ensure that it, together with other members of the National Statistical System, carries out its functions efficiently through the use of modern technologies;

በመሆኑም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55, Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

PART ONE

GENERAL

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የስታቲስቲክስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፭/፪ሺ፲፰ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Ethiopian Statistics Proclamation No. 1435/2026."

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ስታቲስቲክስ"** ማለት ከቆጠራዎች፣ ከናሙና ጥናቶች፣ ከአስተዳደር መዛግብት እንዲሁም ከጂኦስፓሽያል፣ ከዲጂታል ምንጮች፣ ከሴንሰር መሣሪያዎች፣ ከቢግ ዳታ ሥርዓቶች እና ከሌሎች አዳዲስ የዳታ ምንጮች፣ ተጠናቅረው እና ተተንትነው አስተማማኝ ማስረጃዎችን ለማቅረብ በሥርዓት የተደራጀ አሐዛዊ ወይም ዓይነታዊ መረጃ ነው፤

፪/ **"የስታቲስቲክስ ፕሮግራም"** ማለት በሚኒስቴሩ እና በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት በጋራ የሚዘጋጅ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስታቲስቲክስ መስኮችን የሚያመለክት እና በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ የሚከናወኑ የስታቲስቲክስ ተግባራትን በመካከለኛ ዘመን እና በዓመታዊ ፕሮግራሞች ለማቀድ፣ ለማስተባበርና ለመተግበር መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ኦፊሴላዊ ሰነድ ነው፤

፫/ **"የስታቲስቲክስ ጥናት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ለስታቲስቲክስ ዓላማ የሚውል በስታቲስቲክስ አመንጪዎች ከተወሰነ ሕዝብ ውስጥ የስታቲስቲክስ ሥነ-ዘዴን በመጠቀም በዋነኛነት የግል ዳታ ከመልስ ሰጪዎች የመሰበሰብ ተግባር ነው፤

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Statistics"** means systematically organized quantitative or qualitative information obtained from censuses, surveys, administrative records, and other emerging data sources, including geospatial, digital, sensor-based, and big-data systems, processed and analyzed to provide reliable evidence;

2/ **"Statistical Program"** means an official document prepared by the Ministry and the Ethiopian Statistics Service that outlines priority statistical areas and serves as the basis for the planning, coordination, and execution of statistical activities within the National Statistical System, through defined mid-term and annual programs;

3/ **"Statistical Survey"** means the primary collection of individual data from respondents of a given population carried out by a producer of statistics exclusively for statistical purposes through the systematic use of statistical methodology;

፬/ **"የስታቲስቲክስ አሐድ"** ማለት መሠረታዊ የዳታ መሰብሰቢያ መነሻ ወይም የመለኪያ አካል ሆኖ ዳታ የሚሰበሰብበት ወይም የሚገኝበት ተፈጥሯዊ ሰው፣ ቤተሰብ፣ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ወይም ተያያዥ አካል ነው፤

፭/ **"የስታቲስቲክስ ምስጢራዊነት"** ማለት ይፋዊ የስታቲስቲክስ አመንጪዎች በመላው የዳሰሳ ጥናትና መረጃ አሰባሰብ፣ የማከማቸት እና የስርጭት ዑደት ሂደት ውስጥ የግለሰብ መረጃዎችን የመጠበቅ ግዴታቸውን የሚገልጽ አሠራር ነው፤

፮/ **"የስታቲስቲክስ ሬጂስተር"** ማለት ለስታቲስቲክስ ዓላማ የተሰበሰቡ አሐዶች ሲሆኑ፣ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ የአሐዶች መገለጫዎችንም ያካትታል፤

፯/ **"የስታቲስቲክስ አገልግሎቶች"** ማለት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥን፣ የፖሊሲ ቀረጻን፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ፣ የማሕበራዊ እና የሥነ ሕዝብ ለውጦችን ክትትል ለመደገፍ እንዲቻል፣ ዳታን በባለሙያ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተን፣ የመተርጎም እና የማሰራጨት ተግባራት ናቸው፤

፰/ **"ኦፊሽያል ስታቲስቲክስ"** ማለት በተባበሩት መንግሥታት የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ መሠረታዊ መርሖዎች፣ በዓለም አቀፍ ስምምነት በተደረገባቸው የስታቲስቲክስ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች፣ ምክረ ሐሳቦች፣ አግባብነት ካላቸው ሀገራዊ ሕጎችና ፕሮግራሞች ጋር በተጣጣመ መልኩ በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት እና በሌሎች የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች የሚመነጭና የሚሰራጭ ስታቲስቲክስ ነው፤

4/ "**Statistical Unit**" means the elementary observation or measurement unit, namely a natural person, a household, an economic operator or other undertaking for which data are collected or derived;

5/ "**Statistical Confidentiality**" means to the obligation of official statistics producers to protect individual data throughout the entire lifecycle of collection, storage, and dissemination;

6/ "**Statistical Register**" List of units maintained for statistical purposes, including characteristics of the units needed to meet the purposes;

7/ "**Statistical Services**" means the professional collection, organization, analysis, interpretation, and dissemination of data to support informed decision-making, policy formulation, and monitoring of economic, social, and demographic trends;

8/ "**Official Statistics**" means statistics produced and disseminated by the Ethiopian Statistical Service or other producers of official statistics in conformity with the United Nations Fundamental Principles of Official Statistics, internationally agreed statistical standards, codes and recommendations as well as applicable national legislation and programs;

፱/ **"የስታቲስቲክስ ደረጃዎች"** ማለት ኦፊሻያል ስታቲስቲክስን ለማመንጨት እና ለማሰራጨት የሚረዱና ተቀባይነት ያገኙ ደረጃዎች፣ ምደባዎች፣ ጽንሰ-ሐሳቦች፣ ትርጓሜዎች፣ ሥነ ዘዴዎች፣ የሜታ ዳታ ፍላጎቶች፣ የጥራት ማረጋገጫ ማዕቀፎች እና ፕሮቶኮሎች ናቸው፤

9/ "**Statistical Standards**" means standards, classifications, concepts, definitions, methodologies, metadata requirements, quality assurance frameworks, and protocols adopted for the production and dissemination of official statistics;

፲/ **"ዳታ"** ማለት በጥሬው ወይም በተደራጀ መልኩ ከቆጠራ፣ ከናሙና ጥናት፣ ከአስተዳደር መዛግብት ወይም ከማንኛውም ሌላ ምንጭ የተገኘ እና ስታቲስቲክስ ለማመንጨት የሚጠናቀር፣ የሚተነተን እና የሚሰራጭ አሃዛዊ ወይም ዓይነታዊ መረጃ ነው፤

10/ **"Data"** means quantitative or qualitative information in raw or organized form, obtained from censuses, surveys, administrative records, or any other sources, and which may be processed, analyzed, and disseminated to produce statistics;

፲፩/ **"አስተዳደራዊ ዳታ"** ማለት የመንግሥት አካላት ወይም ሌሎች ተቋማት አገልግሎት ሲሰጡ፣ መርሐ ግብሮቻቸውን ሲያከናውኑ ወይም ሕጎችን በማስከበር ሂደት ውስጥ በዋናነት ለስታቲስቲክስ ወይም ለምርምር ዓላማዎች ሳይሆን ለአስተዳደር ወይም ለተግባራዊ ሥራዎች ዓላማ የሚሰበስቡት ዳታ ነው፤

11/ **"Administrative Data"** means data collected by Government organs or other institutions while providing services, executing programs, or enforcing laws, primarily for administrative or operational purposes rather than for statistics or research purposes;

፲፪/ **"ቢግ ዳታ"** ማለት ከንግድ ወይም ከመንግሥታዊ ሥራ እንቅስቃሴዎች፣ ከማሕበራዊ ሚዲያ፣ ከስልክ ምዝገባ ማስታወሻዎች፣ ከመገናኛ መሣሪያዎች፣ ከበይነ መረብ፣ ከሴንሰሮች፣ እና ከመሳሰሉት ምንጮች የሚገኝ እና ከፍተኛ መጠን፣ ፍጥነት እና ተለያይነት ያለው ዳታ ነው፤

12/ **"Big Data"** means data generated by business or Government transactions, social media, phone logs, communication devices, web scraping, sensors, and other similar sources and characterized by high volume, velocity and variety;

፲፫/ **"ዳታ አቅራቢ"** ማለት በዋነኛነት ለግል ፍጆታ የሚውል ዳታን የሚያመነጭ ማንኛውም የመንግሥት ወይም የግል ተቋም ነው፤

13/ **"Data Provider"** means any public or private entity, that produces data primarily for own purposes;

፲፬/ **"አዳዲስ የዳታ ምንጮች"** ማለት በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች፣ በሴንሰሮች፣ በሳተላይት እና ጂኦስፓሽያል ሲስተሞች፣ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች፣ ኦንላይን መድረኮች፣ ማሕበራዊ ሚዲያዎች እና ሌሎች በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ ሂደቶች በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች የሚፈጠሩ አዲስ ወይም ከተለመዱት የመረጃ ምንጮች ውጭ ስታቲስቲክስን ለማመንጨት የሚያገለግልሉ ዳታዎች ናቸው፤

14/ **"Emerging Data Sources"** means new or non-traditional data generated through digital technologies, sensors, satellite and geospatial systems, mobile devices, online platforms, social media, and other technology-based processes that can be used for producing statistics;

፲፭/ **"የግል ዳታ"** ማለት ስለ ስታቲስቲክስ አሐዶች በጥልቀት የቀረበ ዝርዝር ዳታ ነው፤

15/ **"Individual Data"** means the most detailed level of data about statistical units;

፲፮/ **"ሜታ ዳታ"** ማለት በዳታ ይዘት፣ ጥራት፣ ሁኔታ፣ ምንጭ፣ ቅርጽ፣ መዋቅርና ባሕርይ ላይ የሚገኝ መረጃን ጨምሮ ዳታን የሚያብራራ፣ የሚገልጽ፣ የሚለይ፣ ወይም ዳታ መሰብሰብን፣ መጠቀምን፣ ማስተዳደርን፣ ወይም መተርጎምን የሚያቀልል የተቀነባበረ ወይም ያልተቀነባበረ መረጃ ነው፤

16/ **"Metadata"** means structured or unstructured information that describes, explains, identifies, or otherwise makes it easier to collect, use, manage, or interpret data, including information on the content, quality, condition, origin, format, structure, and characteristics of such data;

፲፯/ **"የዳታ ምንጭ"** ማለት በመንግሥታዊ ወይም በግል ተቋማት የሚመነጩትን ጨምሮ ቆጠራዎች፣ የናሙና ጥናቶች፣ የአስተዳደር መዝገቦች፣ የማያቋርጥ የምዝገባ ሥርዓቶች፣ የስታቲስቲክስ ሬጂስተሮች፣ ጂኦስፓሽያል እና ዲጂታል የመረጃ ሥርዓቶች እና ሌሎች አዳዲስ የቴክኖሎጂ ወይም አማራጭ የዳታ ምንጮች ናቸው፤

17/ **"Data Source"** means censuses, sample surveys, administrative records, continuous registration systems, and other emerging technological or alternative data sources, including those generated by public or private entities;

፲፰/ **"ጂኦስፓሽያል ዳታ"** ማለት ከጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ወይም ከቦታ ማጣቀሻ ጋር የተያያዘ፣ ከካርታ ሥራ፣ ከሳተላይት ምስሎች፣ ከሪሞት ሴንሲንግ ወይም ተመሳሳይ ቴክኖሎጂዎች የተገኘ እና ስታቲስቲክስን ለማመንጨት እና ለመተንተን የሚያገለግል ዳታ ነው፤

18/ **"Geospatial Data"** means data that is associated with a geographic location or spatial reference, obtained from mapping, satellite imagery, remote sensing or similar technologies, and used for the production and analysis of statistics;

፲፱/ **"ማይክሮ ዳታ"** ማለት ግለሰቦችን፣ ቤተሰቦችን፣ ተቋማትን ወይም ሌሎች የስታቲስቲክስ አሐዶችን በሚመለከት በቆጠራ፣ በጥናት፣ ከአስተዳደራዊ መዛግብት ወይም ከሌሎች የዳታ ማሰባሰቢያ ሂደቶች የሚሰበሰብ ነጠላ ደረጃ ዳታ ነው፤

19/ **"Microdata"** means a unit-level data collected through censuses, surveys, administrative records or other data collection processes which pertain to individual persons, households, establishments, or other statistical units;

፳/ **"የዳታ ጥራት"** ማለት ዳታዎች እና የስታቲስቲክስ ውጤቶች ለታለመላቸው ዓላማ ብቁ መሆናቸውን የሚያሳይ ደረጃ ሲሆን፣ ይህም በመረጃዎቹ አግባብነት፣ ትክክለኛነት፣ ወቅታዊነት፣ ወጥነት፣ ተነፃፃሪነት እና አስተማማኝነት ይገለጻል፤

20/ **"Data Quality"** means the degree to which data and statistical outputs are fit for their intended use, as reflected by their relevance, accuracy, timeliness, coherence, comparability and reliability;

፳፩/ **"ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት"** ማለት የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎትን እና ኦፊሽያል ስታቲስቲክስን እንዲሰበስቡ፣ እንዲያጠናቅሩ እንዲያመነጩና እንዲያሰራጩ የተፈቀደላቸውን ሌሎች የመንግሥት አካላትን ያካተተ የተቀናጀ የተቋማት ስብስብ ሲሆን፤ ይህም ተግባራቸው የሚመራበትን ሕጋዊ፣ የተቋማዊ እና ቅንጅታዊ አደረጃጀቶችን፣ ደረጃዎችን እና አሠራሮችን ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስ የሚመነጭበትና የሚሰራጭበት ሥርዓት ነው።

21/ **"National Statistical System"** means the integrated set of institutions, including the Ethiopian Statistical Service and other Government organs authorized to collect, compile, produce, and disseminate official statistics, together with the legal, institutional, and coordination arrangements, standards, and procedures governing their activities, through which official statistics are generated and disseminated in Ethiopia;

፳፪/ **"ቻርተር"** ማለት በአፍሪካ ውስጥ ይፋዊ ስታቲስቲክስን ለማመንጨትለማስተዳደር እና ለማሰራጨት የሚያስፈልጉ መርሆዎችን፣ ደረጃዎችን እና ማዕቀፎችን ለመወሰን በአፍሪካ ኅብረት አባል ሀገራት የፀደቀውን የአፍሪካ ስታቲስቲክስ ቻርተር ሲሆን፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚደረግበትን ማሻሻያም ይጨምራል።

22/ **"Charter"** means the African Charter on Statistics, adopted by Member States of the African Union to determine the principles, standards, and frameworks governing the production, management, and dissemination of official statistics in Africa, and includes any amendments made to it from time to time.

፳፫/ **"ቆጠራ"** ማለት ወሰኑ በውል በታወቀ ቦታና በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና የሥነ ሕዝብ ዘርፎች ላይ አጠቃላይ ቆጠራን በማካሄድ መሠረታዊ ዳታዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመገምገምና ውጤቱንም ለተጠቃሚዎች የማሰራጨት ተግባር ነው፤

23/ **"Census"** means the collection, compilation, evaluation and dissemination of basic data pertaining to economic, social and demographic sectors through a complete enumeration of units in a defined scope, place and time frame;

፳፬/ **"የማያቋርጥ ምዝገባ"** ማለት የአስተዳደር መዋቅርን ተከትሎ በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከን ደረጃ በሕጋዊ የማያቋርጥ ምዝገባ ሥርዓት የወሳኝ ኩነቶችን ወይም የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ድርጅቶችን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መመዝገብ ነው፤

24/ **"Continuous Registration"** means the recording of vital events or economic and social establishments, on a continuous basis, by adopting legally prescribed procedures at National, Regional State or lower administrative levels;

፳፭/ **"ማሰራጨት"** ማለት ኦፊሽያል ዳታዎችን፣ የስታቲስቲክስ ትንታኔዎችን፣ የስታቲስቲክስ አገልግሎቶችንና ሜታዳታን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የማድረግ ተግባር ነው፤

25/ **"Dissemination"** means the activity of making official statistics, statistical analyses, statistical services and metadata accessible to users;

፳፮/ **"መለያ"** ማለት የአንድ የስታቲስቲክስ አሐድ በስሙ፣ በትክክለኛ የጂኦግራፊ መገኛ እና የዳታውን ቀጥተኛ በሆነ አንድ ወይም ተያያዥ በሆኑ መለያዎች በማያሻማ ሁኔታ እንዲታወቅ ወይም እንዲለይ የሚያደርጉ ተከታታይነት ያላቸው ምልክቶች ናቸው፤

26/ **"Identifier"** means a sequence of characters allowing direct identification of a statistical unit from one or a combination of identifiers, using its name, exact geographical location or identification number without ambiguity;

፳፯/ **"ሌሎች ኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች"** ማለት ከአገልግሎትቱ በተጨማሪ፣ በሕግ ኦፊሽያል ስታቲስቲክስን እንዲያመነጩ ሥልጣን የተሰጣቸው የመንግሥት አካላት ናቸው፤

27/ **"Other Producers of Official Statistics"** means Government bodies other than the Service authorized by law to produce official statistics;

፳፰/ **"ማመንጨት"** ማለት ስታቲስቲክስን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ዳታን ከመሰብሰብ፣ ከማጠናቀር፣ ከመተንተን እና ከማከማቸት ጋር ተያያዥ የሆኑ ሁሉም ተግባራት ናቸው፤

28/ **"Production"** means all the activities related to collection, processing, analysis and storage of data which are necessary to compile statistics;

፳፱/ **"ታዋቂ ባለሙያ"** ማለት በስታቲስቲክስ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ኢኮኖሜትሪክስ፣ ዴሞግራፊ፣ ዳታ ሳይንስ፣ የዳታ ወይም መረጃ አስተዳደር ወይም በሌሎች ተዛማጅ

29/ **"Renowned Professional"** means a person who possesses recognized professional competence, extensive experience, and demonstrated

ዘርፎች ዕውቅና ያገኘ ሙያዊ ብቃት፣ ሰፊ የሥራ ልምድ እና የተረጋገጠ የአመራር ብቃት ያለው እንዲሁም ከኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስና ከዳታ ሥርዓቶች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከፍተኛ የሙያ ምክርና አመራር መስጠት የሚችል ሰው ነው።

leadership capability in statistics, economics, econometrics, demography, data science, data or information management, or other related fields, and who is capable of providing high-level professional guidance and oversight in matters relating to official statistics and data systems.

፴/ **"ግብዓት"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስን ለማመንጨት፣ ለማቀነባበር፣ ለመተንተን፣ ለማሰራጨት እና ጥራቱን ጠብቆ ለማቆየት የሚያስፈልጉ እና ጥቅም ላይ የሚውሉ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ በጀት፣ የቴክኖሎጂ እና የኮምፒውተር መሠረተ ልማት፣ የመስክ መጓጓዣ እና የቢሮ ቁሳቁሶች፣ የስታቲስቲክስ ስልቶችና መመሪያዎች፣ እንዲሁም ከአስተዳደራዊ መዛግብትና ከሕዝብ የሚሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎችን የሚያጠቃልል ማናቸውም ቁሳዊ እና ኢ ቁሳዊ ሀብት ነው፤

30/ **"Input"** means any tangible or intangible resource required and utilized, pursuant to this Proclamation, for the production, processing, analysis, dissemination, and ensuring the quality of official statistics, including human and financial resources, technology and computer infrastructure, field transportation and office equipment, statistical methodologies and guidelines, as well as raw data collected from administrative records and the public.

፴፩/ **"መልቀቅ"** ማለት የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ የተሻሻለ ስታቲስቲክስን ጨምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ይፋ የሚደረግበት የዳታ ስርጭት ተግባር ነው፤

31/ "**Release**" means the dissemination of official statistics, including revised statistics, to make them publicly known for the first time;

፴፪/ **"መልስ ሰጪ"** ማለት፣ ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ የግል ወይም የመንግሥት ተቋም ሆኖ ስለራሱ እና ተግባሩ በስታቲስቲክስ አመንጪዎች በሚካሄዱ የናሙና ጥናቶች፣ ቆጠራዎች ወይም የማይቋረጡ ምዝገባዎች መረጃ እንዲሰጥ የሚጠየቅ ነው፤

32/ **"Respondent"** means an individual person, a household, a private or public entity that is requested to provide information about themselves, including their activities through sample surveys, census or registration carried out by producers of statistics;

፴፫/ **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ዋና ኃላፊ ነው፣

33/ **"Director General"** means the head of Ethiopian Statistical Service;

፴፬/ **"ለስታቲስቲክስ ዓላማ መጠቀም"** ማለት በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ሁሉንም ተግባራት ጨምሮ ዳታን ለኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ልማት፣ ማመንጨት እና ስርጭት ብቻ መጠቀም ነው፤

34/ **"Use for Statistical Purposes"** means the exclusive use of data for the development, production and dissemination of official statistics, including all activities regulated by this Proclamation;

፴፭/ **"የመንግሥት ተቋም"** ማለት የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ሲሆን የፌደራል ወይም የክልል የልማት ድርጅትን ይጨምራል፤

35/ "**Government Organization**" means any organ of the Federal or Regional State Government and includes a public enterprise owned by the Federal or a Regional Government;

፴፮/ **"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

36/ "**Ministry" or "Minister**" means Ministry or Minister of of Planning and Development, respectively;

፴፯/ "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተቋቋሙትንና በአንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት አዲስ የተደራጁትን ክልሎች፣ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን የሚያጠቃልል ነው፤

37/ **"Region**" means the regions established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and newly organized in accordance with Article 47, Sub-Article (3) letter (e), and the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

፴፰/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

38/ **"Person"** means any natural or legal person;

፴፱/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል።

39/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በሚከተሉት የፌደራል፣ የክልል፣ እና የከተማ አስተዳደር አካላት እና አሠራሮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

፩/ በኦፊሻያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች፤

፪/ በመልስ ሰጪዎች፤

፫/ በአስተዳደራዊ ዳታ አቅራቢዎች፤

፬/ በሁሉም የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ ተጠቃሚዎች፤

፭/ በማንኛውም ስታቲስቲክስ አመንጪ በሆኑ አካላት እጅ የሚገኙ ዳታዎች፣

፮/ በሁሉም የስታቲስቲክስ ጥናቶች እና የቆጠራ እንዲሁም አስተዳደራዊ ዳታ የማመንጨት ሥራዎች፤

፯/ በማያቋርጡ የምዝገባ ሥርዓቶች።

፬. <u>የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ መሠረታዊ መርሐዎች</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተባበሩት መንግሥታት የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ መሠረታዊ መርሐዎች እና የአፍሪካ የስታቲስቲክስ ቻርተር መርሐዎች በዚህ አዋጅ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

፩/ የስታቲስቲክስ ውጤት አግባብነት፣

፪/ የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች ገለልተኝነት

፫/ የስታቲስቲክስ እኩል ተደራሽነት

፬/ የሞያ ደረጃ፣ ሳይንሳዊ መርሐዎችን እና የሞያ ሥነ ምግባርን ተግባራዊ ማድረግ

፭/ ግልጽነት እና ተጠያቂነት

፮/ ስታቲስቲክስን አላግባብ መጠቀምን መከላከል

፯/ የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ ምንጮችን የመምረጥ መብት

፰/ የግለሰብ ዳታ ምስጢራዊነት

3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall apply to the following Federal, Regional and Citiy Administration organs and procedures:

1/ Producers of Official Statistics;

2/ Respondents;

3/ Administrative data providers;

4/ All users of official statistics;

5/ Any data in the possession of producers of statistics;

6/ All statistical surveys and census operations and administrative data production;

7/ Continuous registration systems.

4. <u>Fundamental Principles of Official Statistics</u>

The United Nations Fundamental Principles of Official Statistics and the African Charter on Statistics, listed below, shall also be applicable on this Proclamation:

1/ Relevance of statistical results,

2/ Impartiality of Producers of Official Statistics

3/ Equal Access of statistics

4/ Applying Professional Standards, Scientific Principles, and Professional Ethics

5/ Transparency and Accountability

6/ Prevention of Misuse of Statistics

7/ Right of Selecting Sources of Official Statistics

8/ Confidentiality of Individual Data

፱/ ተቋማዊ ቅንጅት

፲/ የዓለም አቀፍ ደረጃዎችን መጠቀም

፲፩/ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ቅንጅት

፲፪/ ዓለም አቀፋዊና ቀጣናዊ ትብብር

ክፍል ሁለት

የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት አደረጃጀት

፭. አገልግሎቱን እንደገና ስለመቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት (ከዚህ በኋላ "**አገልግሎት**") እየተባለ የሚጠራ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፤

፪/ አገልግሎቱ ለሚኒስቴሩ ተጠሪ ይሆናል።

፮. የአገልግሎቱ አቋም

አገልግሎቱ፦

፩/ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ ሞያዊ መመዘኛና ልምድን መሠረት በማድረግ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፤

፫/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤

፬/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

፯. ዋና መሥሪያ ቤት

የአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

9/ Institutional Coordination

10/ Use of International Standards

11/ Coordination of the National Statistical System

12/ International and Regional Cooperation

PART TWO

ORGANIZATION OF THE NATIONAL STATISTICAL SYSTEM

5. Reestablishment of the Service

1/ The Ethiopian Statistical Service (hereinafter the "**Service**") is hereby reestablished as an autonomous Federal Government organization having its own legal personality;

2/ The Service shall be accountable to the Ministry.

6. Organization of the Service

The Service shall have:

1/ The Ethiopian Statistical Board (hereinafter "the Board");

2/ A Director General to be appointed by the Prime Minister based on professional criteria and experience;

3/ One or more Deputy Directors General appointed by the Prime Minister.

4/ The necessary staff.

7. Head Office

The Service shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices, as may be necessary.

፰. ሳይንሳዊ እና ቴክኒካዊ ነፃነት

የመረጃ ምንጮች፣ የስታቲስቲክስ ዘዴዎችና ሂደቶች ምርጫን፣ ሥርጭትን ወይም የስታቲስቲክስ ምስጢራዊነትን መጠበቅ፣ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን በተመለከተ፣ በአገልግሎቱ፣ በሠራተኞቹ ወይም በሥሩ በሚገኙ ፈጻሚ የሥራ ክፍሎች ተግባራት ላይ በማንኛውም ሰው ያልተገባ ተጽዕኖ ሊደረግ አይችልም።

8. Scientific and Technical Independence

No undue influence may be exerted in the affairs of the Service; its staff or its implementing units by any person in technical matters regarding data sources; the selection of statistical methods and procedures, dissemination, or observance of statistical confidentiality.

፱. የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ቦርድ

፩/ የቦርዱ አባላት፡-

ሀ) ቦርዱ የአገልግሎቱን ዋና ዳይሬክተር ሳይጨምር ፱ (ዘጠኝ) አባላትይኖሩታል፤

ለ) የቦርዱ አባላት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሳይወሰን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1) የመንግሥት አካላት፤
2) የአካዳሚክ እና ምርምር ተቋማት፤
3) የግል ሴክተር ተወካዮች፤
4) የሞያ ማኅበራት፤
5) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፤
6) ታዋቂ ግለሰቦች፤

ሐ) የቦርዱ አባላት አካታችነትን ወይም የጾታ ተዋጽኦን ያገናዘበ ሆኖ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ተቋማት የሚመረጡት የቦርድ አባላት በስታቲስቲክስ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ሥነ ሕዝብ ጥናት፣ ዳታ ሳይንስ ወይም ተዛማጅ ዘርፎች የሚገኙ ታዋቂ ባለሞያዎች መሆን አለባቸው፤

መ) የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፤

9. The Ethiopian Statistical Board

1/ Composition of the Board:

a) The Board shall have 9 (Nine) members without including the Director General of the Service;

b) The composition of the Board includes, but not limited to the following:

i) Government Organs;
ii) Academic and Research Institutions;
iii) Private Sector representatives;
iv) Professional Associations;
v) Civil Society Organizations;
vi) Renowned Professionals;

c) Taking into account inclusiveness or gender representation in the composition of the Board, members of the Board elected from the above entities shall be professionals with recognized expertise in statistics, economics, population studies, data science, or related fields;

d) The term of service for members of the Board shall be Three years;

ሠ) የቦርድ አባላት ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፤

፪/ የቦርዱ ሰብሳቢ፡-

ሀ) የቦርዱ ሰብሳቢና ሌሎች የቦርድ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማሉ፤

ለ) ሰብሳቢው በቦርዱ አጀንዳዎች ላይ ስትራቴጅክ አመራር ይሰጣል፤ የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፤

፫/ የቦርዱ ጸሐፊ፡-

ሀ) አገልግሎቱ የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

ለ) የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ ጸሐፊና ድምጽ አልባ አባል ይሆናል፤

ሐ) ጸሐፊው የቦርዱን ውሳኔዎች ትግበራ ያስተባብራል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፬/ ቦርዱ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም የቦርዱ ሰብሳቢ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ቢያንስ አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የቦርዱ አባላት ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤ የቦርዱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ሪፖርት አቀራረብ እንዲሁም ሌሎች አሠራሮቹን አስመልክቶ ዝርዝሩ በደንብ ይገለጻል።

e) Members of the Board may not be elected for more than Two consecutive terms;

2/ Chairperson of the Board:

a) The Chairperson and other members of the Board shall be appointed by the Prime Minister;

b) The Chairperson shall give strategic direction on the agenda of the Board and chairs its meetings;

3/ Secretary of the Board:

a) The Service shall serve as the Secretariat of the Board;

b) The Director General of the Service shall be the Secretary and a non-voting member of the Board;

c) The Secretary shall coordinate and follow up the implementation of decisions of the Board;

4/ The Board shall convene quarterly. However, the Chairperson of the Board may convene an extraordinary meeting on his own initiative or upon the request of at least one-third of the members of the Board; Particulars regarding procedures of the Board's meetings, its decision making, reporting, and other related activities shall be determined by Regulation.

፲. የቦርዱ ሥልጣን እና ኃላፊነቶች

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የብዝሀ ዓመታት ብሔራዊ ስታቲስቲክስ ልማት ፕሮግራምን፣ የአገልግሎቱን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅዶችን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ የዳታ ጥራት ግምገማ ማዕቀፍንና የብሔራዊ ስታቲስቲክስ መልቀቂያ ሠሊዳን ጨምሮ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችና መስፈርቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣ ያጸድቃል፣ ያስተባብራል፤

፪/ ስታቲስቲክስን በሚመለከቱ ጉዳዮች አገልግሎቱን እና የሌሎች ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት አባላት የአሠራርና ሞያዊ ነጻነት ያረጋግጣል፣ ከአላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ይከላከላል፤

፫/ በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ የስታቲስቲክስ እንቅስቃሴዎችን በማስተባበርና በመቆጣጠር ወጥነትና ተስማሚነት ያላቸው እና ስምምነት ከተደረሰባቸው ዓለም አቀፍ የስታቲስቲክስ ደረጃዎች ጋር ተስማሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፬/ የስታቲስቲክስ ሥራዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራትና ሥርዓቱን ለማስተባበር ከተዛማጅ ተቋማት የተውጣጡ የዘርፍ የስታቲስቲክስ አስተባባሪ ኮሚቴዎችን እና የቴክኒክ የሥራ ቡድኖችን በማቋቋም ሥራቸውን በበላይነት ይመራል፤

10. Powers and Responsibilities of the Board

The Board shall have the following powers and responsibilities:

1/ Ensure, approve and coordinate the implementation of the Multi-annual National Statistical Development Program, the strategic plan of the Service, annual statistical work plans, and national statistical priorities and standards, including the Ethiopian Data Quality Assessment Framework and the National Statistics Release Calendar;

2/ Ensure the operational and professional autonomy of the Service and other members of the National Statistical System, and protect them from undue external interference;

3/ Oversee and coordinate statistical activities across the National Statistical System to ensure consistency, harmonization, and adherence to internationally agreed statistical standards;

4/ Oversee and lead the activities of Sectoral Statistics Coordination Committees and Technical Working Groups composed of relevant institutions, to effectively manage statistical activities and coordinate the System;

፭/ በተዘረጉ አሠራሮችና ፕሮቶኮሎች መሠረት በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ ቅንጅት እንዲፈጠር ማበረታታት እና ቀልጣፋ የዳታ መጋራትና መስተጋብር እንዲኖር ያመቻቻል፤

፮/ በአዳዲስ የዳታ አሰባሰብ ዘዴዎች፣ በቴክኖሎጂና እና በምርጥ ልምዶች አተገባበር እና በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ልማት ላይ ስትራቴጂክ አመራር ይሰጣል፤

፯/ በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን እና ቀጣይነት ያለው መሻሻልን ለማረጋግጥ፣ በስታቲስቲክስ አሠራሮች እና አፈጻጸሞች ላይ በየጊዜው የአቻ ግምገማዎችን ያመቻቻል፣ አስፈላጊ ከሆነም ገለልተኛ የግምገማ ቡድኖችን በማቋቋም ተዓማኒነትንና ቀጣይነት ያለውን ማሻሻያ ያደርጋል፤

፰/ ኦፊሽያል ስታቲስቲክስ የሚያመንጩ የመንግሥት ተቋማት የስታቲስቲክስ ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍል እንዲያቋቁሙ ያደርጋል፤

፱/ ሀብት ማሰባሰብን አስመልክቶ ስልታዊ አጋርነቶችን ያጠናክራል፤

፲/ ቦርዱ ሪፖርቱን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ያቀርባል።

፲፩. <u>የሚኒስቴሩ ሥልጣን እና ኃላፊነቶች</u>

ሚኒስቴሩ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት ሚናዎች እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

5/ Promote institutional cooperation and facilitate effective data sharing and interoperability among National Statistical System members, in accordance with established procedures and protocols;

6/ Provide strategic leadership on the adoption of innovative data collection methods, technology and best practices and generally on the Ethiopian statistics development;

7/ To ensure transparency, accountability and continuous improvement within the National Statistical System, conduct regular peer reviews on statistical practices and performances, where necessary, by establishing independent evaluation teams to guarantee credibility and continuous improvement;

8/ Require Government institutions that produce official statistics to establish a unit that deals with statistical activities.

9/ Strengthening strategic partnerships for resource mobilization.

10/ The Board reports to the Office of the Prime Minister.

11. <u>Powers and Responsibilities of the Ministry</u>

The Ministry shall have the following powers and responsibilities regarding the National Statistical System;

፩/ በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ የስታቲስቲክስ ተግባራትን የሚመለከቱ ሕጎች እና የሥነ ምግባር መርሖዎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሕጎቹ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፪/ የብዝሀ ዓመታት የስታቲስቲክስ ልማት ፕሮግራሞችን ንድፍና ዝግጅት ያስተባብራል፤ ከብሔራዊ የልማት ግቦች እና ከዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር ያላቸውን መጣጣም ያረጋግጣል፤

፫/ የብዝሀ ዓመታት የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞችን አገልግሎቱን በማሳተፍ ያዘጋጃል፣ በቦርድ ያስጸድቃል፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፬/ በኦፊሽያልና በሌሎች ስታቲስቲክስ አመንጪዎች የሚቀርቡ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ የሥራ መርሐ-ግብሮችን ከብሔራዊ የልማት ቅድሚያዎች እና ከብዝሀ ዓመታት የስታቲስቲክስ ልማት ማዕቀፍ ጋር መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፣ ይገመግማል፤

፭/ ከአገልግሎቱ ጋር በመመካከር፤በመንግሥት አካላት መካከል ወጥ የሆነ የመረጃ መረብ እንዲኖር በማበረታታት፣ የጋራ የዳታ ልውውጥ ደረጃዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ በመደገፍ እና የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎችን ቅንጅት ተግባራትን በማስተባበር፣ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ተቀናጅቶ እንዲሠራ ያመቻቻል፤

1/ Ensure compliance of applicable laws and codes of practice governing statistical activities within the National Statistical System; submits legal amendment to the concerned body, when necessary;

2/ Coordinate the design and preparation of multi-annual statistical development programs; and ensure their alignment with national development goals and international obligations;

3/ Prepare multi-annual statistical programs by involving the Service, get them approved by the Board, and follow up their implementation;

4/ Review annual statistical work programs submitted by producers of official and other statistics to ensure their alignment with national development priorities and the multi-annual statistical development framework;

5/ Facilitate the integration of the National Statistical System by promoting a unified information network across Government bodies, supporting the adoption of common data exchange standards, and coordinating interoperability across producers of official statistics, in consultation with the Service;

፮/ የብዝሀ ዓመታት የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞችን የመካከለኛ እና የመጨረሻ ጊዜ ግምገማዎች እንዲካሄዱ ያመቻቻል፤

፯/ የኦፊሻያል እና ሌሎች የስታቲስቲክስ አመንጪዎች የተቋቋሙ ደረጃዎችን እና የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ የሥነ ምግባር ሕጎችን ማክበራቸውን ለማረጋገጥ ተግባሮቻቸውን በኦዲት፣ ግምገማዎች እና ምዘናዎች ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፰/ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ የመልቀቂያ ጊዜ ሠሌዳን ትግበራ ይቆጣጠራል፣ ድንጋጌዎቹ መከበራቸውን ይከታተላል፤ ከብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎች እና ዕቅዶች ጋር ያለውን ወጥነት እና መጣጣም ያረጋግጣል፤

፱/ የኢትዮጵያ የዳታ ጥራት ቁጥጥር ማዕቀፍ፣ በሁሉም አግባብነት ባላቸው የስታቲስቲክስ ሥራዎች ላይ መተግበሩን ያረጋግጣል፤

፲/ የሁሉም ኦፊሻያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞች ወጥ፣ ያልተደጋገሙ፣ በግለሰቦች፣በቤተሰቦች፣ በንግድ ወይም በሌሎች ተቋማት ላይ አላስፈላጊ የምላሽ ጫና እንዳይፈጥሩ ለማድረግ የሁሉንም ኦፊሻያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎችስታቲስቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፤ ያስተባብራል፤

6/ Facilitate mid-term and end-term evaluations of multi-annual statistical programs to be conducted;

7/ Oversee and assess the activities of producers of official and other statistics through audits, reviews, and evaluations to ensure their compliance with established standards and the Code of Practice for Official Statistics;

8/ Oversee the implementation of the national statistical statistics calendar, monitor the observance of its provisions, ensure its consistency, and alignment with national development plans;

9/ Ensure the implementation of the Ethiopian Data Quality Assessment Framework across all relevant statistical operations;

10/ Oversee and coordinate the statistical activities of all producers of official statistics to ensure that statistical programs are harmonized, do not duplicate, and do not impose unnecessary response burden on individuals, households, businesses, or other institutions;

፲፩/ ኦፊሽያል ስታቲስቲክስ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሥርዓት እና በሌሎች የሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው ዓለም አቀፍ መስፈርቶች፣ ምደባዎች እና ሥነ ዘዴዎች መሠረት መመንጨት እንዲችል፤ ከአገልግሎቱ ጋር በመተባበር የስታቲስቲክስ ትርጓሜዎችን እና ምደባዎችን ጨምሮ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ፖሊሲዎችን እና መስፈርቶችን ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል፣ ያስፈጽማል፤

11/ Develop, approve, and enforce national statistical policies and standards in collaboration with the Service, including statistical definitions and classifications, to ensure that official statistics are produced in accordance with internationally recognized standards, classifications, and methodologies of the United Nations system and other relevant international organizations;

፲፪/ በፖለቲካዊ እና በዲፕሎማሲያዊ ደረጃ ከስታቲስቲክስ አስተዳደር እና ልማት ጋር በተያያዙ ዓለም አቀፍ መድረኮች እና በብይነ መንግሥታት አካላት በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ሀገሪቱን ይወክላል።

12/ Represent the country in international forums and intergovernmental bodies concerned with statistical governance and development at the political and diplomatic level.

፲፪. <u>የአገልግሎቱ ሥልጣን፣ ኃላፊነቶችና ተግባራት</u>

12. <u>Powers,Responsibilities and Functions of the Service</u>

አገልግሎቱ:-

The Service shall:

፩/ በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት ደረጃዎች እና አሠራሮች መሠረት በኢኮኖሚ፣ በማሕበራዊ፣ በሥነ ሕዝብ፣ በባሕል፣ በከባቢ፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና ሌሎች ተዛማጅ መስኮች የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ዳታዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

1/ Collect, compile, analyze, and disseminate official statistical data on the economic, social, demographic, cultural, environmental, scientific, technological, and other relevant areas, in accordance with the standards and procedures of the National Statistical System;

፪/ በሕግ በተደነገጉ የዳታ እና የግል ዳታ ጥበቃ መስፈርቶች መሠረት በመንግሥት ወይም በግል አካላት የመነጩ ዳታዎችን ከቆጠራ፣ ከናሙና ጥናቶች፣ ከአስተዳደር መዛግብት፣ ከቢግ ዳታ፣ ከማያቋርጥ የምዝገባ ሥርዓቶች፣ ከስታቲስቲክስ

2/ Access data generated by public or private entities, subject to the data and personal data protection requirements prescribed by law and such data may include information from censuses, sample surveys, administrative

ሬጂስተሮች፣ በጂኦስፓሻያል እና ከዲጂታል የመረጃ ሥርዓቶች እንዲሁም ከሌሎች ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ወይም አማራጭ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎችን ማካተት አለበት፤

records, big data sources, continuous registration systems, statistical registers, geospatial and digital information systems, and other modern technological or alternative sources;

፫/ በቦርዱ ከጸደቁ ፖሊሲዎችና መስፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ፣ እንዲሁም ኦፊሻያል ስታቲስቲክስን ለማመንጨት ከሚረዱ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ መርሖዎች ጋር የተናበቡ ተገቢ የሆኑ የስታቲስቲክስ ዘዴዎችን፣ ትርጓሜዎችን፣ ምደባዎችንና ቴክኒካዊ መስፈርቶችን ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነታቸውንም ያረጋግጣል፤

3/ Establish, implement, and enforce appropriate statistical methods, definitions, classifications, and technical standards, consistent with the policies and standards approved by the Board, and aligned with national and international norms governing the production of official statistics;

፬/ በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ ሀገራዊ የስታቲስቲክስ መስፈርቶችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ እንዲሁም የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ ዳታን በማመንጨት፣ በማጠናቀር እና በማሰራጨት ሂደት ውስጥ እነዚህ መስፈርቶች ወጥ በሆነ መልኩ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

4/ Implement national statistical standards across the National Statistical System and ensure their uniform application in the production, compilation, and dissemination of official statistical data;

፭/ የኢትዮጵያ የዳታ ጥራት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ማሻሻያዎችን አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ያስጸድቃል፤ በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ በሚከናወኑ የስታቲስቲክስ ተግባራት ላይ በወጡት ደረጃዎች መሠረት የዳታ ጥራት ማረጋገጫ ግምገማዎችን ያካሂዳል፤

5/ Prepare revisions of the Ethiopian Data Quality Assurance Framework and submit them to the Board for approval, and shall conduct data quality assurance assessments on statistical activities within the National Statistical System in accordance with established standards;

፮/ የስታቲስቲክስ ግንዛቤና አጠቃቀም በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓትና በሕብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ ያበረታታል፤

6/ Promote statistical literacy and the effective use of statistics within the National Statistical System and the general public;

፯/ ለመንግሥት እና ለሌሎች አካላት አስተዳደራዊ ዳታ አያያዝ እና የዳታ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ላይ የአቅም ግንባታ፣ የቴክኒክ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤

7/ Provide capacity building, technical support and advice for Government and other bodies on administrative data management and data reporting system;

፰/ በአገር ውስጥ የሚሰበሰበውን የስታቲስቲክስ ዳታ ከሌሎች አገሮች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተቋማት የስታቲስቲክስ ዳታ ጋር ማነፃፀር በሚያስችል መልኩ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸውን ደረጃዎች፣ ምደባዎች እና ዘዴዎችን በመጠቀም መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤

8/ Ensure that domestic statistical data are produced in a manner that enables comparability with the statistical data of other countries, international organizations, and the United Nations organs, through adoption of internationally recognized standards, classifications, and methodologies;

፱/ ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር የብሔራዊ ስታቲስቲክስን የመልቀቂያ ጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፣ በየጊዜው ያሻሽላል፤

9/ Prepare and periodically update the National Statistical Statistics Calendar, in comsultation with the Ministry;

፲/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስን አግባብነት እና ጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የስታቲስቲክስ ዳታ የሚፈለግባቸውን መስኮች እና ተገቢ የዳታ ማጠናቀር ሂደቶችን በተጠቃሚዎችና አመንጪዎች የምክክር መድረክ በኩል ከተጠቃሚዎች ጋር በመመካከር፣ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ቅድሚያዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይወስናል፤

10/ Determine the areas for which statistical data are required and the appropriate data compilation procedures, in consultation with users through the User-Producers Consultation Forum, taking into account national and international priorities to ensure the relevance and usefulness of official statistics;

፲፩/ ሀገራዊ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ዳታ ማከማቻ ማዕከል በመሆን ያገለግላል፤ የዳታ ማከማቻ ቋት በዋና መሥሪያ ቤት ያደራጃል፣ አቅሙንም ያሻሽላል፤

11/ Serve as national data storage center for official statistics, organize data storage center at the head office and improve its capacity;

፲፪/ ከስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻያል ኢንስቲትዩት ወይም ከሌላ ተመሳሳይ ተቋም ጋር በመቀናጀት የጂኦስፓሻያል ዳታዎችን ለስታቲስቲክስ ዓላማ ይሰበስባል፤ የስታቲስቲክስ ዳታዎችን ወደ ዲጂታል እና ጂኦስፓሻያል ፎርማት በመቀየር በሥዕላዊ መንገድ ያቀርባል፣ ያሰራጫል፤

12/ In coordination with the Space Science and Geospatial Institute, or any other similar institution, collect geospatial data for statistical purposes, and convert statistical data to digital and geospatial formats to facilitate data visualization and dissemination;

፲፫/ በስታቲስቲክስ ሥነ ዘዴዎች ላይ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ የተገኙት ውጤቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያበረታታል፤

13/ Undertake studies and research on statistical methods and promote the utilization of the results thereof;

፲፬/ በሳይንሳዊ ምርምር ቴክኒኮች፣ ዘዴዎች እና የመረጃ ቴክኖሎጂዎች ረገድ በስታቲስቲክስ መስክ የተደረጉ ዕድገቶችን በመከታተል የተደረጉ የዕድገት ለውጦችን ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

14/ Monitor advancements in scientific research techniques, methods, and information technologies in the field of statistics, and take appropriate measures to adopt and implement such advancements;

፲፭/ ጥያቄ ሲቀርብለት የስታቲስቲክስ ዳታ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን፣ ትንተናን፣ ህትመትን እና ስርጭትን ጨምሮ የስታቲስቲክስ ሥራዎችን በማቀድ፣ በማስተባበር እና አፈጻጸም ላይ ለክልሎች እና ለከተማ አስተዳደሮች የቴክኒክና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤

15/ Provide technical assistance and advice to Regional States and City Administrations in planning, coordination, and execution of statistical activities, regarding collection, organization, analysis, publication, and dissemination of statistical data, upon request;

፲፮/ በክልላዊ መንግሥታት እና ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የስታቲስቲክስ ምዝገባ ሥርዓቶችን መዘርጋት እና ማጠናከር ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ደረጃዎች እና ልምዶች ጋር እንዲጣጣም ያደርጋል፤

16/ Follow up and support the establishment and strengthening of statistical registration systems in Regional States and City Administrations to ensure alignment with National Statistical System Standards and practices;

፲፮/ ከዕቅዶቹና ከፕሮግራሞቹ ወሰን ውጪ የሆኑ ልዩ ጥናቶችን ለማድረግ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከመንግሥት ተቋማት እና ሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል፤

፲፯/ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ዳታ ጥራት፣ ቅንጅት እና ፈጠራን የማጠናከር ዓላማ ያለው የስታቲስቲክስ የልህቀት ማዕከል በሥሩ ያቋቁማል፤ የልህቀት ማዕከሉም በኦፊሻያል ስታቲስቲክስ ሥነ ዘዴ የምርምር እና የአቅም ግንባታ እና ምርጥ ተሞክሮዎች ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

፲፰/ ከሚመለከታቸው የዘርፍ ስታቲስቲክስ አካላት ጋር በመተባበር የዓመታዊ ዝርዝር የሥራ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፤ ፕሮግራሞችን ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ ያደራጃል፤ እንዲሁም ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ተደራሽነታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፱/ ለስታቲስቲክስ ዓላማዎች የአስተዳደራዊ ዳታዎችን እና የስታቲስቲክስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቶችን በመንደፍ፣ በመንግሥት ተቋማትና በሌሎች ድርጅቶች እንዲተገበሩ ድጋፍ ይሰጣል፤

፳/ በስታቲስቲክስ እና በተዛማጅ ዘርፎች ከሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የሞያ ማሕበራት ጋር በመተባበር እንደ አስፈላጊነቱ የስታቲስቲክስ ኮንፈረንሶችን ስፖንሰር ያደርጋል፤

17/ Cooperate with International organization, Government institutions and other organizations, to undertake specific surveys outside the scope of its plans and programs;

18/ Establish a Statistical Center of Excellence within its institutional framework with the objective of strengthening the quality, coordination, and innovation of the Ethiopian Statistical System. The center shall serve as a hub for methodological research, capacity building, and best practices in official statistics;

19/ In collaboration with relevant sectoral statistical bodies, shall prepare detailed annual work plans, organize programs in a technical manner, and ensure their accessibility by making them public;

20/ Design administrative data and statistical reporting systems for statistical purposes to be followed by Government agencies and other organizations and assist their implementation;

21/ Collaborate with national and international professional associations in the fields of statistics and related disciplines to sponsor statistical conferences; as appropriate;

፳፪/ በዳታ አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ለምርምር፣ ለትምህርት ወይም ለሀገራዊ ጠቀሜታ ከመንግሥታዊ ድርጅቶች እና በነፃ እንዲወስዱ ከተፈቀደላቸው በስተቀር የጥናትና ቆጠራ ጥሬ ዳታን ለመስጠት ክፍያዎችን ሊያስከፍል ይችላል፤ በመሆኑም የክፍያ ተመኖችን፣ ዓይነቶችን እና ዝርዝር አፈጻጸሙን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤

22/ May charge fees for the provision of raw survey and census data, in accordance with the microdata access guidelines, except where such data are provided free of charge to Government institutions or to persons authorized to obtain them free of charge for research, educational purposes, or for the national interest. The fee rates, categories, and detailed modalities for implementation shall be prescribed by a Regulation to be issued by the Council of Ministers;

፳፫/ የመንግሥት ተቋማት የየራሳቸውን ስታቲስቲክስ ክፍሎች እንዲያቋቁሙ ይመክራል፣ ይደግፋል፤

23/ Advise and support Government institutions to establish their respective statistical units;

፳፬/ በሁሉም የስታቲስቲክስ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤

24/ Advise the Government on all matters of statistics;

፳፭/ ለኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ውጤቶች ሳይንሳዊ እና ቴክኒካዊ ማብራሪያዎችን ይሰጣል፤

25/ Provide scientific and technical explanations to the results of official statistics;

፳፮/ ኦፊሽያል ስታቲስቲክስን ለማልማት፣ ለማመንጨት እና ለማሰራጨት በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ውስጥ የሚተገበሩ መመሪያዎችን ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር ያወጣል፤

26/ Issue Directives to be applied across the National Statistical System for the development, production and dissemination of official statistics, in consultation with the Ministry;

፳፯/ የስታቲስቲክስ፣ የዳታ አሰባሰብ እና ቅንብር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

ሀ) ጥያቄ ሲቀርብለት፣ ለስታቲስቲክስ ዓላማ ከተሰበሰቡ በእጁ ከሚገኙ ዳታዎች ላይ በሐቀኝነት፣ በጥራት፣ በተዓማኒነት እና በምስጢራዊነት መርሖዎች መሠረት የስታቲስቲክስ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

27/ Provide statistical, data collection and compilation services;

a) Upon request, provide statistical data collection, and compilation services utilizing data under its possession, in accordance with the principles of quality, integrity, credibility, and confidentiality of official statistics;

ለ) ከገንዘብ ፍሰት ጋር የተያያዙ እና በተለያዩ ፕሮግራም ፈንዶች ውስጥ የሚተገበሩ የፕሮግራም ውጤት አመላካቾች የማረጋገጥ ተግባራትን ያከናውናል፤

ሐ) በሚሰጠው ግልጋሎት ምክንያት የሚያወጣቸውን ተጨማሪ ወጪዎች ለመሸፈን ተጠቃሚዎችን በደንብ የሚገለጽ ተመጣጣኝ ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፤

መ) የስታቲስቲክስ አገልግሎትን አስመልክቶ ዝርዝር ሂደቶች እና የአፈጻጸም ዘዴዎች በደንብ ይገለጻሉ፤

፳፰/ በዓለም አቀፍ ትብብሮች ስለመሳተፍ፡-

ሀ) ባለው ሞያዊ የብቃት ከባቢ፣ የስታቲስቲክስ ደረጃዎችና ምክረ ሀሳቦችን ለማሻሻልና ለመተግበር በዓለም አቀፍ አውደጥናቶች እና ጉባዔዎች ላይ ይሳተፋል፤

ለ) ከኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ጋር ተያይዞ በሚደረጉ ማንኛውም ዓለም አቀፍ የቴክኒክ ትብብሮች ላይ ይወከላል፤

ሐ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የሴክተር ቴክኒካዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ፣ ሌሎች የሚመለከታቸው የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊሳተፉ ይችላሉ፤

፳፱/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎችን ዝርዝርን ወቅታዊ ያደርጋል፤

b) Conduct program verification for results of program indicators that are linked with cash flow and implemented under different funds;

c) May charge reasonable fees to cover additional costs incurred in preparing and providing access to such data, as will be determined by Regulation;

d) Detailed procedures and implementation modalities for the provision of such services shall be determined by Regulation;

28/ Participation in International cooperation:

a) In its areas of competence, shall participate in international workshops and conferences to develop and implement statistical standards and recommendations;

b) be the focal point for all international technical cooperation activities concerning statistics;

c) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (b), other producers of official statistics may participate at international level regarding sectoral technical matters;

29/ Update the list of producers of official statistics;

፴/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ወይም የአስተዳደራዊ ዳታ ዕቅድን፣ ማመንጨትን፣ ማጣጣምን፣ ልውውጥን እና ስርጭትን በተመለከተ ከክልል የስታቲስቲክስ አመንጪ ተቋማት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

፴፩/ የስታቲስቲክስን ትክክለኛ አተረጓጎም ያመቻቻል፣ ኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አላግባብ ጥቅም ላይ ሲውል ወይም ሲተረጎም በይፋ አስተያየቱን ይሰጣል፤

፴፪/ ሌሎች የአገልግሎቱን ሥልጣንና ኃላፊነቶችን የተመለከቱ ዝርዝሮች በደንብ ይገለጻሉ።

፲፫. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

ዋና ዳይሬክተሩ፡-

፩/ የአገልግሎቱ ዋና የሥራ ኃላፊ በመሆን የአገልግሎቱን ተግባራት ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ውስጥ የተገለጹትን የአገልግሎቱን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፤

ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የአገልግሎቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የሥራ መርሐ ግብሮችንና በጀትን እንዲሁም የአገልግሎቱን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

መ) ለአገልግሎቱ በተፈቀደው የሥራ ፕሮግራም እና በጀት መሠረት ወጪዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

30/ Shall work in cooperation with the regional producers of statistics in the planning, production, harmonization, exchange, and dissemination of official statistics or administrative data;

31/ Facilitate the correct interpretation of statistics and comment publicly on any misuse or misinterpretation of official statistics;

32/ Details regarding other powers and responsibilities of the Service shall be determined by a Regulation.

13. Powers and Duties of the Director General

The Director General shall:

1/ Be the head of the Service and shall direct and administer the activities of the Service;

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Exercise the powers and duties of the Service stated in this Proclamation;

b) Recruit and administer employees of the Service in accordance with the Federal civil service laws;

c) Prepare and submit to the Ministry the work programs and budget as well as the activity reports of the Service;

d) Effect expenditure in accordance with the work program and budget approved for the Service;

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደረገው ግንኙነት ሁሉ አገልግሎቱን ይወክላል፤

፫/ ለአገልግሎቱ ቀልጣፋ አስተዳደር ሲባል ከሥልጣኑ እና ከሥራው የተወሰነውን ክፍል፣ አስፈላጊ በሆነ መጠን ለአገልግሎቱ ባለሥልጣናት እና ለሌሎች የአገልግሎቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፬/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ስልታዊ ልማትን በማበረታታት፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን እና አጋርነትን በማጎልበት፣ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስን አግባብነት፣ ጥራት እና ተፅዕኖውን ለማሳደግ አመራር ይሰጣል፤

፭/ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓትን በዓለም አቀፍ ደረጃ በመወከል ዓለም አቀፍ የስታቲስቲክስ አጋርነትን እና ትብብርን ያመቻቻል፤

፮/ ግልጽና በሰነድ የተደገፉ የአሠራር ሂደቶችን በመከተል፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ሥር በተደነገጉት መሠረታዊ መርሖዎች መሠረት፤ የሌሎች አመንጪዎች ዳታ እና ተግባራት በኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስ ዝርዝር ወይም ምድብ ውስጥ እንዲካተቱ ለቦርዱ የቴክኒክ ምክርና የውሳኔ ኃሳብ ይሰጣል፤

፯/ በኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ውስጥ በዳታ አቅራቢዎች የሚተገበሩ እንደ ጽንሰሐሳቦች እና ትርጓሜዎቻቸው፣ ስያሜ እና ኮድ እና ምደባዎች ያሉ የስታቲስቲክስ ደረጃዎች አጠቃቀምን ያሳድጋል፤

e) Represent the Service in all its dealings with third parties;

3/ May delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Service to the extent necessary for the efficient management of the Service;

4/ Provide leadership in the strategic development of official statistics and in fostering partnership and stakeholder engagement to enhance its relevance, quality, and impact;

5/ Represent the National Statistical System at the international level and facilitate international statistical cooperation and collaboration;

6/ Provide technical advice and recommendations to the Board on the inclusion of data and activities of other producers in the list or category of official statistics, in accordance with the Fundamental Principles set forth under Article 4 of this Proclamation and through transparent and documented procedures;

7/ Promote the use of the statistical standards such as concepts and their definitions, naming and coding and classifications applied in official statistics by data providers;

፲፬. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

፩/ በስራቸው የሚገኙትን የሥራ ክፍሎች ተግባራት ያስተባብራሉ፣ ይመራሉ፤

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ በሌለበት እና ለእያንዳንዳቸው ተለይቶ በተሰጣቸው የሥልጣን ውክልና መሠረት እንደ ዋና ዳይሬክተር ሆነው ይሠራሉ፤ እንዲሁም

፫/ በዋና ዳይሬክተሩ የተሰጣቸውን ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናሉ።

14. <u>Powers and Duties of the Deputy Director Generals</u>

The Deputy Director Generals shall:

1/ Coordinate and direct the activities of the departments or units under their respective supervision;

2/ In the absence of the Director General, act on his behalf and on the basis of specific delegation of powers given to each of them; and

3/ Perform any other activities assigned to them by the Director General.

፲፭. <u>ሌሎች የኦፊሻያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች ተግባራት</u>

፩/ በአገልግሎቱ የማይሰበሰቡ የዘርፍ ዳታዎችን በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ደረጃዎች መሠረት ያመነጫሉ፤

፪/ የዘርፍ ዳታዎች አስተማማኝነት እንዲኖራቸው የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ደረጃዎችን፣ መርሖዎችን እና ሂደቶችን በመከተል ተግባራቸውን ያከናውናሉ፤

፫/ ዘርፍ ተኮር ዳታዎች በሀገሪቱ የዳታ ማጋራት ሕጎች መሠረት ወቅታዊነታቸውን፣ ትክክለኛነታቸውንና ተዓማኒነታቸውን በጠበቀ መልኩ መሰብሰባቸውን፣ ሪፖርት መደረጋቸውን እና መጋራታቸውን ያረጋግጣሉ፤

፬/ ከአገልግሎቱ ጋር በመተባበር የስታቲስቲክስ ዘዴዎችን እና የብሔራዊ ስታቲስቲክስ አሰራሮችን ያሻሽላሉ፤

15. <u>Duties of Other Producers of Official Statistics</u>

1/ Generate sector-specific data that are not generated by the Service in accordance with National Statistical System statistical standards;

2/ Comply with National Statistical System's statistical standards, principles, and procedures, to ensure the reliability of sector-specific data;

3/ Ensure that sector-specific data are collected, reported, and shared in a timely, accurate, and reliable manner, in accordance with national data-sharing laws;

4/ In collaboration with the Service, improve statistical methods and national statistical practices;

፭/ በየዘርፎቻቸው የሚከናወኑ የስታቲስቲክስ አሠራሮች ከሀገራዊና ከዓለም አቀፋዊ መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲሻሻሉና እንዲቀናጁ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፤

፮/ ከአገልግሎቱ እና ከሚኒስቴሩ ጋር በመተባበር በስታቲስቲክስ ዘዴ ልማት እና በዳታ ማመንጨት እንቅስቃሴዎች ላይ የየዘርፎቻቸው አስተዋፅኦዎች ከብሔራዊ ግቦች ጋር እንዲጣጣሙ ያደርጋሉ።

5/ Contribute to the improvement and harmonization of statistical practices within their respective sectors in accordance with national and international standards;

6/ In collaboration with the Service and the Ministry, ensure each sector's contributions to the development of statistical methods and data production activities are aligned with national goals.

፲፮. <u>በጀት</u>

የአገልግሎቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች ይገኛል፤ በጀቱም በመንግሥት የበጀት አስተዳደር ሕግ ይመራል።

፩/ በመንግሥት የሚመደብ በጀት፤

፪/ አገልግሎቱ ከሚሰጣቸው ሥልጠናዎችና ሌሎች አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ ክፍያዎች፤

፫/ ከሌሎች ሀገሮች አቻ ተቋማትና ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች የሚያገኛቸው የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የቴክኒክ ድጋፎች።

16. <u>Budget</u>

The budget of the Service shall be obtained from the following sources; The implementation of budget is according to the Government laws of budget administration.

1/ Budget allocated by the Government;

2/ Revenue collected from training fees and other service charges;

3/ Financial, material and technical support from other countries' peer institutions and international development partners.

፲፯. <u>የአገልግሎቱ ሠራተኞች አስተዳደር</u>

የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፫/፪ሺ፲፯ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩/ አገልግሎቱ ለሥራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መዋቅራዊ አደረጃጀት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤

17. <u>Administration of employees of the Service</u>

Notwithstanding the provisions of the Federal Civil Servants Proclamation No. 1353/2025:

1/ the Service may undertake and implement organizational structure study as may be appropriate for its functions;

፪/ አገልግሎቱ የሠራተኞችን ደሞዝና ጥቅማጥቅም በማጥናት ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል።

፲፰. <u>የሂሳብ መዝገብ</u>

፩/ አገልግሎቱ ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪/ የአገልግሎቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየሙ ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራል።

<u>ክፍል ሦስት</u>
<u>የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞችና ዳታ ማመንጨት</u>

፲፱. <u>የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞች</u>

፩/ ከሀገራዊ የልማት ዕቅዶች እና ከዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር የተጣጣመ፣ መካከለኛ ዘመንና ብዝሀ ዓመታት ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም፣ ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ልማት፣ ቅንጅታዊ አሠራር እና አተገባበር እንደ መሪ ማዕቀፍ ሆኖ ይቀረጻል፤

፪/ ፕሮግራሙ፣ የተቋማዊ እና የሰው ኃይል አቅምን በማጠናከር፣ የመረጃ ሥርዓቶችን እና ቅንጅትን በማሻሻል፣ እንዲሁም በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥን ለመደገፍ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን በማበረታታት፣ አስተማማኝ፣ የተቀናጀ እና ጥራቱን የጠበቀ የስታቲስቲክስ ሥርዓት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ይቀረጻል፤

2/ the Service shall study salary scale and employment benefit schemes for its employees; implement same when approved.

18. <u>Books of Accounts</u>

1/ The Service shall keep accurate and complete books of accounts;

2/ The books of accounts and financial documents of the Service shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

<u>PART THREE</u>
<u>STATISTICAL PROGRAMS AND DATA PRODUCTION</u>

19. <u>Statistical Programs</u>

1/ A mid-term and multi-annual national statistical program, aligned with national development plans and international commitments, shall be formulated as the leading framework for the development, coordination, and implementation of the national statistical system;

2/ The Program shall be designed to ensure the establishment of a reliable, integrated, and high-quality statistical system by strengthening institutional and human capacity, improving data systems and coordination, and promoting the use of modern technologies to support evidence-based decision-making;

፫/ በቦርዱ የፀደቁ የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞች የመንግሥት ፕሮግራሞች ተደርገው ይወሰዳሉ፤

፬/ ለኦፊሻል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች ለፕሮግራሞቹ ውጤታማ አተገባበር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ይሟሉላቸዋል፤

፭/ የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞችን ዝግጅት፣ አፀዳደቅ እና አፈጻጸም በተመለከተ ዝርዝር የአሠራር ሂደቶች በደንብ ይወሰናሉ።

3/ Statistical programs approved by the Board shall constitute Government programs;

4/ Producers of official statistics shall be provided with the necessary resources for their effective implementation;

5/ Detailed procedures for the preparation, approval, and execution of statistical programs shall be determined by Regulation.

፳. <u>ዳታ ማመንጨት</u>

፩/ ኦፊሻል ስታቲስቲክስን ለማመንጨት የሚውሉ ዳታዎች፣ ከቆጠራዎች፣ ከናሙና ጥናቶች፣ ከአስተዳደራዊ መዝገቦች፣ ከቢግ ዳታ፣ ከዲጂታል፣ ከጂኦስፓሻል እንዲሁም ከሌሎች ዘመናዊ ወይም አማራጭ የዳታ ሥርዓቶችን ከመሳሰሉ የታመኑ ምንጮች፣ ከታወቁ ደረጃዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ ይሰበሰባሉ፤

20. <u>Data Production</u>

1/ Data for the production of official statistics shall be collected from appropriate sources, including censuses, sample surveys, administrative records, big data sources, and digital, geospatial, and other modern or alternative data systems, in accordance with established standards and procedures;

፪/ ኦፊሻል ስታቲስቲክስን ማመንጨት፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን የሚመለከቱትን ጨምሮ ዕውቅና ያላቸውን ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ምደባዎችን እና ደረጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ፣ የመረጃዎችን ወጥነት እና ተነጻጻሪነት ማረጋገጥ አለበት፤

2/ The production of official statistics shall ensure consistency and comparability through the application of recognized national and international classifications and standards, including those relating to economic activities;

፫/ አገልግሎቱና ሌሎች ኦፊሻል ስታቲስቲክስ አመንጪ ተቋማት የግለሰቦች ማንነት ያልተገለፀበትን ዳታ በስታቲስቲክስ ፕሮግራሞቻቸው በተጠቀሰው መሠረት በየራሳቸው ኃላፊነት መስክ ኦፊሻል ስታቲስቲክስን ለማልማት፣

3/ The Service and other producers of official statistics are entitled to exchange anonymized individual data, exclusively for the development, production and dissemination of official statistics, in

ለማመንጨት እና ለማሰራጨት ብቻ መለዋወጥ ይችላሉ፤

፬/ ማንኛውም በሀገር አቀፍ ደረጃ የስታቲስቲክስ ጥናት ለማካሄድ ያቀደ አካል፤ ጥናቱን ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት አገልግሎቱን ማማከር እና በስታቲስቲክስ ጥናት ዘዴው ላይ የአገልግሎቱን ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፤

፭/ ዳታ ማመንጨትን፣ ማቀናጀትን እና ዳታ ማጋራትን የሚመለከቱ ዝርዝር አሠራሮች በደንብ ይገለጻሉ።

፳፩. <u>የአስተዳደራዊ ዳታ ተደራሽነት</u>

፩/ የመንግሥት አካላት ወይም ሌሎች ተቋማት ኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ለማመንጨት አስፈላጊ የሆኑ አስተዳደራዊ ዳታዎችን እና ተዛማጅ ሜታዳታዎችን ለሚመለከታቸው የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች በነፃ ማቅረብ አለባቸው። የቀረበው አስተዳደራዊ ዳታ እና ሜታዳታ ጥራትን የሚያረጋግጥ እና አስፈላጊውን ዝርዝር ማካተት አለበት፤

፪/ የአስተዳደራዊ ዳታ አቅራቢዎች አዲስ የዳታ አሰባሰብ ዘዴ ለማዘጋጀት ወይም የኦፊሽያል ስታቲስቲክስን ከማመንጨት ጋር የሚገናኝ የዳታ አሰባሰብ ዘዴዎቻቸው ወይም አሠራራቸው ላይ ክለሳ ከማካሄዳቸው በፊት ከአገልግሎቱ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚኒስቴሩ ጋር መመካከር አለባቸው።

their respective area of competence as indicated in their statistical programs;

4/ Any person who intends to conduct a national level statistical survey shall consult the Service and obtain approval on the statistical survey methodology prior to implementation;

5/ Detailed procedures governing data production, coordination, and data-sharing shall be determined by Regulation.

21. <u>Access to Administrative Data</u>

1/ Government organs or other institutions shall provide administrative data and the corresponding metadata to the relevant Producers of Official Statistics free of charge, for the production of official statistics. The administrative data and the metadata provided shall include sufficient details to ensure quality;

2/ Administrative data providers, prior to planning to develop a new data collection method or carry out a major revision in their data collection methods or processing in relation to production of Official Statistics, they shall consult the Service and, where appropriate, with the Ministry.

፳፪. ቆጠራ

፩/ የሕዝብ፣ የቤት፣ የሕንፃ፣ የኢኮኖሚ ድርጅቶች፣ የግብርና ሥራዎችን ጨምሮ በሌሎች የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ቆጠራ ሊካሄድ ይችላል፤

፪/ የቆጠራ ዳታ ከአጠቃላይ ቆጠራ፣ ከናሙና ጥናቶች፣ ከአስተዳደር መዛግብት ወይም ከእነዚህ የዳታ ምንጮች ጥምረት በመጠቀም ሊሰበሰብ ይችላል፤

፫/ መልስ ሰጪዎች ወይም ዳታ አቅራቢዎች ለቆጠራ የሚፈለገውን ትክክለኛ ዳታ በወቅቱ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፤

፬/ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራዎች "የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፱/፩ሺ፱፻፺፯" መሠረት ይተዳደራሉ፤

፭/ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ላልሆኑ ሌሎች ቆጠራዎች ወይም ግዙፍ ጥናቶች ሥራን ለማስተባበር፣ ሚኒስቴሩ ከአገልግሎቱ ጋር በመመካከር ዓብይ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል።

፳፫. የስታቲስቲክስ ሬጅስተር

፩/ አገልግሎቱ የሚከተሉትን ያካተተ የስታቲስቲክስ ሬጂስተር ያቋቁማል፤ ያጠናክራል፡-

ሀ) አጠቃላይ የስታቲስቲክስ አሐዶችን፤

ለ) ከስታቲስቲክስ ሬጂስተር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ባሕሪያት፣ መለያዎችን፣ ዓይነቶችን ወይም መገለጫዎችን፤ እና

22. Census

1/ Censuses may be conducted on different topics, encompassing population, housing, building, economic establishments, and agricultural operations;

2/ Census data may be collected through complete enumerations, sample censuses, administrative records, or combination of these data sources;

3/ Respondents or data providers are obligated to provide correct data for census operations on time;

4/ Population and Housing Census operations shall be regulated by "Census Commission Reestablish ment Proclamation No. 449/2005";

5/ The Ministry, in consultation with the Service may establish a Steering Committee for coordinating operations of other types of censuses or large scale surveys.

23. Statistical Registers

1/ The Service shall establish and maintain statistical registers, which shall consist of:

a) comprehensive statistical units;

b) associated attributes or identifiers or types or expressions of statistical registers; and

ሐ) ለስታቲስቲክስ ተግባር ብቻ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸውን እና ኦፊሽያል ስታቲስቲክስንለማመንጨት የሚያስፈልጉ መለያዎችን፤

፪/ በአገልግሎቱ ሥር የሚገኙ ማንኛውም የስታቲስቲክስ ሬጂስተር ዳታዎች ምስጢራዊነት ጥብቅ በሆነ ሁኔታ ይጠበቃሉ፤

፫/ የስታቲስቲክስ ሬጅስተርን ወቅታዊ ለማድረግ የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ፣ ማንኛውም ተቋም በዚህ አዋጅ በተዘረዘሩት የስታቲስቲክስ አሠራር ዘዴዎች እና ደረጃዎች መሠረት የተጠየቀውን ዳታ ለአገልግሎቱ በወቅቱ መስጠት አለበት።

፳፬. <u>የመልስ ሰጪዎች ግዴታዎች</u>

፩/ መልስ ሰጪዎች ስለሚሰጡት የስታቲስቲክስ ዳታ ዓላማ፣ ወሰን፣ ሕጋዊነት፣ ጥቅሙን፣ የዳታ ምስጢራዊነትን ለማረጋገጥ የተወሰዱ እርምጃዎች እና ዳታ የመስጠት ግዴታን እንዲረዱት ይደረጋል፤

፪/ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ የግል እና የመንግሥት ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች መልስ ሰጪዎች በስታቲስቲክስ ጥናቶች እና ቆጠራዎች ላይ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፤

፫/ በስታቲስቲክስ ጥናቶች እና ቆጠራዎች ላይ መልስ ሰጪዎች የሚሰጡት መረጃ ትክክለኛ፣ በተጠየቀው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚቀርብ፣ በሚፈለገው ቅጽ የቀረበ እና ከክፍያ ነፃ መሆን አለበት፤

c) essential identifiers required for production of official statistics which shall be utilized only for statistical purposes;

2/ Statistical registers under possession of the Service shall be protected under strict confidentiality;

3/ All institutions, including Government entities, shall provide the Service the requested data for the purpose of updating statistical register on timely basis by adhering to the prescribed methodologies and standards outlined in this Proclamation.

24. <u>Duties of Respondents</u>

1/ Regarding the data they provide, respondents shall be informed about the purpose, scope, legality, importance, measures taken to ensure confidentiality of data, and obligation to provide data;

2/ Individuals, households, private and public entities and other respondents shall cooperate with statistical surveys and census activities;

3/ Information provided by respondents in statistical surveys and censuses shall be correct and submitted within the required timeframe, in the required format and free of charge;

፬/ መልስ ሰጪዎች የተሳሳተ መረጃ ከሰጡ፣ ወይም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊውን መልስ ካልሰጡ፣ በዚህ አዋጅ የቅጣት ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣሉ።

4/ If respondents provide falsify information, or fail to respond within the specified timeframe, they shall be held liable in accordance with the penalty provisions of this Proclamation.

ክፍል አራት
የስታቲስቲክስ ምስጢራዊነት እና የግል ዳታ አያያዝ

PART FOUR
STATISTICAL CONFIDENTIALITY AND HANDLING OF INDIVIDUAL DATA

፳፭. የስታቲስቲክስ ምስጢራዊነት

፩/ በስታቲስቲክስ ተግባር የተገኘ የግለሰብ ዳታ ለስታቲስቲክስ ዓላማ ብቻ የሚያገለግል ሲሆን፣ በማንኛውም ሀገራዊ ወይም የዓለም አቀፍ ተቋማት ዘንድ ለምርመራ፣ ለደህንነት፣ ለሕግ ወይም ለአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ አይውልም፤

፪/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች ለስታቲስቲክስ ዓላማዎች አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ምስጥራዊነቱን በጠበቀ መንገድ የግለሰብ ዳታዎችን ከመለያዎቻቸው ጋር ማቀነባበር እና ማከማቸት ይችላሉ፤

፫/ የግለሰቦችን መለያዎች የያዙ ሁሉም የዳታ መሰብሰቢያ ቅጾች ለስታቲስቲክስ ዓላማዎች አስፈላጊነታቸው እንዳበቃ ወዲያውኑ መወገድ አለባቸው።

25. Statistical Confidentiality

1/ Individual data obtained by statistical activity shall be used exclusively for statistical purposes and cannot be used for any investigation, security, legal or administrative decision-making by any national or international institution;

2/ Producers of Official Statistics may process and store individual data with identifiers with strict confidentiality so long as necessary for statistical purposes;

3/ All data collection forms that contain identifiers shall be destroyed immediately after their importance for statistical purposes ceases.

፳፮. የግለሰብ ዳታዎችን ይፋ ማድረግ

፩/ አንድን ግለሰብ ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል የስታቲስቲክስ መረጃ ሊገለጽ የሚችለው መረጃው እንዲገለጽ ግለሰቡ በማያሻማ ሁኔታ ፈቃዱን የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፤

26. Release of Individual Data Sets

1/ Statistical information, which enables to identify an individual may be disseminated only if that individual has unambiguously given his consent to the disclosure;

፪/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች መለያዎቻቸው የተወገዱላቸውን ወይም ግለሰቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊለዩ በማይችሉበት ሁኔታ ማንነታቸው የተደበቀላቸውን፣ የግለሰብ ዳታ ስብስቦችን ይፋ ማድረግ ይችላሉ፤

፫/ ግለሰቡ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳይታወቅ ለመከላከል፣ ከሌሎች በይፋ ከሚገኙ መረጃዎች ጋር ማዛመድን ጨምሮ በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሁሉም አግባብነት ያላቸው ጥንቃቄዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

፳፯. <u>ማይክሮ ዳታን ስለማግኘት</u>

፩/ የተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች የማይክሮ ዳታ የማግኘት መመሪያን መሠረት በማድረግ የግለሰቦችን ማንነት የደበቀ ማይክሮዳታን ማግኘት ይችላሉ፤

፪/ ዳታን ማግኘት የሚቻለው ለተፈቀደው ዓላማ አግባብነት ባላቸውና አስፈላጊ በሆኑ መረጃዎች ላይ ብቻ ሆኖ፤ ግለሰቦችን ወይም ተቋማትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መለየት የሚያስችሉ ማንኛቸውንም መለያዎችን ማካተት የለበትም፤

፫/ ተመራማሪዎቹ የግለሰብ ዳታን ላልተፈቀደላቸው አካላት ማስተላለፍ ወይም ግለሰቦችን ቀጥተኛ ባልሆነ ዘዴ ለመለየት በሚያስችል ሁኔታ የተጠቃለለ ዳታን ባለማውጣት የምስጢራዊነት እና የዳታ ጥበቃ ግዴታዎችን ማሟላት አለባቸው፤

2/ Producers of Official Statistics may release sets of individual data if the identifiers are removed or they have been anonymized so that individuals cannot be identified directly or indirectly;

3/ To prevent an indirect identification of an individual, the necessary cautions shall be taken of all relevant means that might reasonably be used, including matching individual data with other publicly available information.

27. <u>Access to Microdata</u>

1/ Authorized users may access anonymized microdata held by the Service or other Producers of Official Statistics in accordance with microdata access guidelines;

2/ Access shall be limited to data relevant and necessary for the approved purpose, excluding all personal identifiers and any information that may permit direct or indirect identification of individuals or entities;

3/ Researchers granted access shall not disclose individual data or derived aggregates that could lead to identification, and shall comply with all confidentiality and data protection requirements.

፳፰. ሥራን ለንዑስ ውል ተቀባይ መስጠት

፩/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች ስታቲስቲክስ ከማመንጨት ወይም ከድጋፍ ሰጪ ተግባራት ጋር የተያያዙ ሥራዎችን በከፊል ለንዑስ ውል ተቀባይ ማስተላለፍ ይችላሉ፤ ይኸም የስታቲስቲክስ ምስጥራዊነት እና የሙያ ደረጃን በጠበቀ ሁኔታ መሆን አለበት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሥራ የተሰጠው ንዑስ ውል ተቀባይ ተግባሩን መፈጸም ያለበት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረታዊ መርሖዎች እና በሌሎች የስታቲስቲክስ ማመንጨት መሥፈርቶች መሠረት ብቻ ነው።

ክፍል አምስት

የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ጥራት፣ አለቃቀቅና ስርጭት

፳፱. የዳታን ጥራት ስለማረጋግጥ

፩/ ጥራትን ለማረጋገጥ ሲባል ኦፊሽያል ስታቲስቲክስ መመንጨትና መሰራጨት ያለበት የተጣጣሙ ደረጃዎችንና ዘዴዎችን በመጠቀም በኦፊሽያል ስታቲስቲክስ ወሰን፣ ጽንሰ ሐሳቦች፣ ትርጓሜዎች፣ አሐዶች እና ምደባዎች መሠረት መሆን አለበት፤

፪/ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች በስታቲስቲክስ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ምንጮችንና ዘዴዎችን እንዲሁም የተገኙትን የዳታ ስብስቦች ደረጃውን በጠበቀ መንገድ ማደራጀት አለባቸው።ተጠቃሚዎች ስታቲስቲክስን ለማመንጨት የሚረዱ ምንጮችና

28. Sub Contracting

1/ Producers of official statistics may subcontract parts of the tasks related to producing statistics or support activities to a subcontractor only when statistical confidentiality and professional independence are ensured;

2/ The subcontractor who is given a task according to Sub-Article (1) of this Article shall perform its activities as per the fundamental principles under Article 4 and other requirements of this Proclamation.

PART FIVE

QUALITY, RELEASE AND DISSEMINATION OF OFFICIAL STATISTICS

29. Ensuring Data Quality

1/ To guarantee quality, official statistics shall be produced and disseminated by using harmonized standards and methods on the basis of the scope, concepts, definitions, units and classifications of official statistics;

2/ Producers of official statistics shall document sources and methods used in the production process, as well as the resulting datasets, in a standardized way. Users shall be kept informed about the sources and methods of producing statistics and

ዘዴዎች እንዲሁም ስለ ስታቲስቲክስ ውጤቶች ጥራት በሜታዳታ አማካኝነት እንዲረዱ ይደረጋል፤

፫/ የኦፊሻል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች የዳታ አያያዝ ሥርዓቶቻቸው ውስጥ በኢትዮጵያ የዳታ ጥራት ግምገማ ማዕቀፍ ላይ የተመሠረቱ የዳታ ጥራት ቁጥጥር ዘዴዎችን ያደራጃሉ፣ ይተገብራሉ፣ ያሻሽላሉ፣ ያጠናክራሉ።

quality of statistical outputs through metadata;

3/ Producers of official statistics shall establish, implement, maintain and strengthen data quality control mechanisms based on Ethiopian Data Quality Assessment Framework in their built in data management systems.

፴. የጥራት ግምገማ

30. Quality Assessment

፩/ የኦፊሻል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች ግብረ መልስ ለመቀበል እንዲያስችላቸው ለተጠቃሚዎች እና መረጃ ሰጪዎች የምክክር መድረኮችን በየጊዜው በማዘጋጀት የሚገኘውን ግብረ መልስ ኦፊሻል ስታቲስቲክስን ለማሻሻልና የዳታ ጥራትን ለማሳደግ መጠቀም አለባቸው፤

1/ Producers of official statistics shall regularly organize consultative forums for users and respondents to provide feedbacks, and shall use such feedbacks in the improvement of official statistics and the quality of data;

፪/ የኦፊሻል ስታቲስቲክስ አመንጪዎች የኦፊሻል ስታቲስቲክስን ጥራትለማሻሻል ከከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ከስታቲስቲክስና ተዛማጅ ሞያ ማህበራት፣ ከሌሎች አገሮች ስታቲስቲክስ ተቋማት፣ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ሊተባበሩ ይችላሉ፤

2/ Producers of Official Statistics may collaborate with higher education and research institutions, statistical or related professional associations, other countries' statistical agencies, and relevant national and international organizations to improve the quality of official statistics;

፫/ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ የዳታ ጥራት ግምገማ ማዕቀፍ እና ራሱ ባዘጋጃቸው የዳታ ጥራት ግምገማ ምክረ ሐሳቦች ላይ ተመሥርቶ በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት አባላት የመነጩ እና የተሰራጩ ኦፊሻል ስታቲስቲክስ ጥራትን በተመለከተ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፤

3/ The Service, based on Ethiopian Data Quality Assessment Framework and recommendations on data quality assessment conducted by itself, shall report to the Board on the quality of official statistics developed and disseminated by members of the National Statistical System;

፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በቦርዱ ሲፈቀድ፣ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ አመንጪዎች ተቋማዊ አሰራር፣ የሥራ ሂደት እና የስታቲስቲክስ ውጤቶችን በተመለከተ በዳታ ጥራት መገምገሚያ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ ዳሰሳ ወይም ግምገማ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ባለሞያዎች ሊከናወን ይችላል።

4/ Regarding the institutional environment, work process and statistical results of the producers of official statistics, an assessment may be conducted, where necessary, based on data quality requirements, by domestic or foreign professionals, with the consent of the Board.

፴፩. <u>የመለቀቂያ ጊዜ ሠሌዳ ማዘጋጀት እና ማሰራጨት</u>

31. <u>Establishment and Publication of Release Calendar</u>

፩/ አገልግሎቱ ከሚኒስቴሩ ጋር ኦፊሻል ስታቲስቲክስ የሚለቀቅባቸውን ቀናት የሚገልጽ የቅድሚያ መልቀቂያ ጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፣ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

1/ The Service in collaboration with the Ministry shall establish and publicly disseminate an advance release calendar specifying the dates for the release of Official Statistics;

፪/ የኦፊሻል ስታቲስቲክስ መልቀቂያ የጊዜ ሠሌዳ በኢትዮጵያ በጀት ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ውስጥ በሚኒስቴሩና በአገልግሎቱ ኦፊሻል ድረ ገጽ እንዲሁም ሌሎች ተገቢ የመገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለበት፤

2/ The release calendar of official statistics shall be publicized in the first quarter of Ethiopian Fiscal Year and It shall be readily accessible through the Minister's and the Service's official website and other appropriate channels of communication;

፫/ በኦፊሻል ስታቲስቲክስ መልቀቂያ ጊዜ ሠሌዳ ላይ ያልተጠበቁ ለውጦች ከተከሰቱ ግልጽ እና አሳማኝ ምክንያቶችን በመስጠት አስቀድሞ ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለበት፤

3/ In case of unforeseen alterations to the release calendar of official statistics, a prior public announcement shall be made by giving clear and cogent reasons;

፬/ ኦፊሻል ስታቲስቲክስ ቀደም ሲል በተገለጸው ቀን ይፋ በማድረግ ሁሉም ተጠቃሚዎች በአንድ ጊዜ ዳታውን እንዲያገኙ ይደረጋል።

4/ Official Statistics shall be released at the pre-announced date, thereby ensuring simultaneous access for all users.

፴፪. <u>የስታቲስቲክስ ዳታዎችን መልቀቂያ ሂደቶች</u>

፩/ አገልግሎቱ የስታቲስቲክስ ዳታዎችን ለማሰራጨት ይፋዊ የማሰራጫ መንገዶችን ያደራጃል፣ በተገቢው ሁኔታም ይይዛቸዋል፤

፪/ የስታቲስቲክስ ዳታዎች በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉና ለአጠቃቀም ምቹ በሆኑ እና የማጠቃለያ ሰንጠረዦችንና ቻርቶችን ባካተቱ ተጠቃሚዎች ተጨማሪ ትንተና እንዲያካሂዱ በሚያስችሉ ዝርዝር መረጃዎች በግልጽና በማሽን ሊነበቡ በሚችሉ ይዘቶች ይለቀቃሉ።

33. <u>Dissemination Policies and Practices</u>

1/ The Ministry in consultation with the Service, shall develop and regularly update a comprehensive dissemination policy that outlines its strategies for effectively reaching diverse user groups;

2/ The Service shall enhance statistical literacy among the public through educational initiatives through clear and concise communication of statistical concepts.

34. <u>Compliance with International Standards and Transparency Obligations</u>

1/ The Ministry shall ensure that dissemination practices and metadata conform to internationally recognized statistical standards and quality frameworks, providing transparent information on data sources, methods, classifications, and data quality, including any revisions or corrections made to previously released Statistical Data.

፪/ ሚኒስቴሩእና አገልግሎቱ ስለስታቲስቲካዊ ዳታ እርማቶችና ማሻሻያዎች በግልጽ መልኩ በማስታወቅ እና በማሰራጫ ሥርዓቶች ላይ ተጠቃሚዎች ግብረ መልስ እንዲሰጡ የሚያስችሉ አሠራሮችና ግልጽ ሂደቶችን ያመቻቻሉ፤ እነዚህም ግብረ መልሶች በተገቢው ሁኔታ እንዲገመገሙና በቀጣይ እንዲታዩ ይደረጋሉ።

2/ The Ministry and the Service shall maintain transparent procedures by clearly communicating revisions to Statistical Data, and by establishing mechanisms for users to provide feedback on dissemination practices, which shall be duly reviewed and considered.

ክፍል ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART SIX
MISCELLANEOUS PROVISIONS

፴፭. የወንጀል ተጠያቂነት

፩/ የአገልግሎቱ ሠራተኛ የሆነ ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፡-

ሀ) በሥራው ምክንያት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያገኛቸውን ምስጢራዊ መረጃዎች ከዚህ አዋጅ ወይም በሥሩ ከሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ጋር በሚጻረር መንገድ ከተጠቀመ፤

ለ) በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድና ከሕግ አግባብ ውጭ ምስጢራዊ መረጃዎችን ካሰራጨና ለሌሎች አሳልፎ ከሰጠ፤

ሐ) ሐሰተኛ የስታቲስቲክስ መረጃ ካጠናቀረ ወይም ከሰጠ ወይም የስታቲስቲክስ ቅጾችን በፈጠራ ዳታ የሞላ እንደሆነ፤

ከሰባ ሺ ብር (ሰላሳ ሺህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ የእስር ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

35. Criminal Liability

1/ A person who is employee of the Service intentionally or by negligence:

a) Uses confidential information he gets directly or indirectly by virtue of his task, in contravention of this Proclamation or Regulations or Directives hereunder;

b) Without lawful authority disseminates or gives confidential information to others;

c) Compiles or issues false statistical information, or complete statistical forms with fabricated data;

Shall be punishable by a fine not exceeding Birr 30,000 (Thirty Thousand) or by imprisonment for a term not exceeding Six months, or by both.

፪/ ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት የአገልግሎቱ ወይም የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪ ሠራተኛ ሥራውን እንዳይሠራ ከከለከለ፤ ወይም ካሰናከለ፤ በማስመሰል የአገልግሎቱ ሠራተኛ ሊባል ከሞከረ፤ የተሳሳተ መረጃ ከሰጠ ከ፵ሺ ብር (አርባ ሺህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስር ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

2/ Any person who, intentionally or by negligence, prevents or obstructs an employee of the Service or a producer of official statistics from performing his duties, falsely represents himself to be an employee of the Service, or provides false information, shall be punishable by a fine not exceeding Birr 40,000 (Fority Thousand) or by imprisonment for a term not exceeding One year, or by both;

፫/ ዳታ ወይም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት የተፈጥሮ ሰው የአገልግሎቱን ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ተግባሩን እንዳያከናውን ከከለከለ፤ ሐሰተኛ መረጃ ከሰጠ፤ ከ፲ሺ ብር (ዐሥር ሺህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ ጥፋቱን የፈጸመው የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ከሆነ ከ፷ሺ ብር (ስልሳ ሺህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

3/ A natural person who is under an obligation to provide data or information and who, intentionally or negligently, prevents an employee of the Service from carrying out his duties, or provides false information, shall be punishable by a fine not exceeding Birr 10,000 (Ten Thousand) where the offence is committed by a juridical person, it shall be punishable by a fine not exceeding Birr 60,000 (Sixty Thousand);

፬/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰበሰበን ዳታ የያዘ ሰነድ ያለሕግ አግባብ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ካጠፋ ወይም ካበላሸ ከ፵ሺ (አርባ ሺህ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስር ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

4/ Any person who, without lawful authority, intentionally or through negligence, destroys or damages a document containing data collected in accordance with this Proclamation shall be punishable by a fine not exceeding Birr 40,000 (Fority Thousand) or by imprisonment for a term not exceeding One year, or by both.

፭/ ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፡-

ሀ) በአገልግሎቱ ወይም በኦፊሽያል ስታቲስቲክስ አመንጪ የተሰጠ ማንኛውንም ሰነድ አስመስሎ የሠራ፤ በሀሰት ያዘጋጀ ወይም የለወጠ እንደሆነ፤

ለ) ለማታለል ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ፣ የሀሰት ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ሆነ ብሎ ያቀረበ ወይም ያሳተመ ወይም ይፋዊ የስታቲስቲክስ ሪፖርቶችን ወይም መዝገቦችን የለወጠ እንደሆነ፤

ሐ) በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድን እውነተኛ እንደሆነ አድርጎ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ እንደሆነ፤

በሕግ ተጠያቂ ሆኖ፤ እንደ ነገሩ ሁኔታ ከ፶ሺ ብር (ሃምሳ ሺህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

5/ Any person who intentionally or by negligence:

a) forges, counterfeits, or alters any document issued by the Service or a Producer of Official Statistics;

b) intentionally presents or publishes false statistical information with the intent to deceive or obtain an improper advantage, or alters official statistical reports or record;

c) uses or attempts to use a forged document as if it were genuine;

Shall be held liable in accordance with the law and shall, depending on the circumstances of the case, be punishable by a fine not exceeding Birr 50,000 (Fifty Thousand) or by rigorous imprisonment for a term not exceeding One year, or by both.

፴፮. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

፩/ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፪/፩ሺ፱፻፺፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

፪/ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ወ) እና አንቀጽ ፶፮ ተሽረዋል።

36. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ Central Statistics Authority Establishment Proclamation No. 442/2005 is hereby repealed;

2/ Sub-Article (1) Paragraph (S) of Article 28 and Article 56 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021 is hereby repealed.

፫/ ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፴፯. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፤

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንቦችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

፴፰. <u>የክልሎች ኃላፊነቶች</u>

፩/ ክልሎች የራሳቸውን የስታቲስክስ ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ፤

፪/ የክልሎች የስታቲስክስ ሕጎች በዚህ አዋጅ ከተካተቱት የኦፊሽያል ስታቲስክስ መሠረታዊ መርሖዎች እና ደረጃዎች የተጣጣሙ ወይም ይበልጥ ጥብቅ የሆኑ ደረጃዎችን የያዙ መሆን አለባቸው፤

፫/ ክልሎች ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓት ተፈጻሚነት መተባበር አለባቸው።

3/ Any law, Regulation, Directive or practice inconsistent with this Proclamation is inapplicable regarding matters provided herein.

37. <u>Power to Issue Regulations and Directives</u>

1/ The Council of Ministers may issue Regulations that may be necessary for the implementation of this Proclamation;

2/ The Ministry may issue Directives that may be necessary for the implementation of this Proclamation and the Regulations issued under the Proclamation.

38. <u>Responsibilities of Regions</u>

1/ Regions may issue their own statistics law;

2/ Regional statistics laws shall be consistent with the fundamental principles of official statistics and the standards included in this Proclamation, or shall contain stricter standards;

3/ Regional States shall cooperate in the implementation of the National Statistical System.

፴፱. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበሩት ሕጎች የተገኙ መብቶችና ግዴታዎች ይህንን አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ሊቀጥሉ ይችላሉ።

39. <u>Transitional Provisions</u>

Rights and duties arising under the provisions of the repealed laws may continue so long as they do not contravene this Proclamation.

፵. <u>አዋጁ የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

40. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፪ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም.

ታዬ አጽቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Done at Addis Ababa, On this 7th day of September, 2026

TAYE ATSKE SELASSIE
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA